King County

# የእርስዎ መረጃ። የእርስዎ መብቶች። የኛ ኃላፊነቶች.

**የግል ጉዳይ ተግባራት ማስታወቅያ**
**የኪንግ ካውንቲ የባህሪ ጤና ድርጅት**

***ተፈፃሚ የሚሆንበት ቀን: ኤፕሪል 1, 2016***

ይህ ማስታወቅያ እርስዎን የሚመለከት ህክምናዊ መረጃ እንዴት ጥቅም ላይ እንደሚውልና እንዴት ፋ ሊሆን እንደሚችል እንዲሁም ደግሞ እርስዎ ይህን መረጃ እንዴት ማግኘት እንደሚችሉ ይገልፃል። ይህ ማስታወቅያ በተጨማሪም እርስዎን የሚመለከት የአበረታች እና አደንዛዥ ንጥረነገሮች መጠቀም ችግር መረጃ እንዴት ጥቅም ላይ እንደሚውልና እንዴት ይፋ ሊሆን እንደሚችል እንዲሁም ደግሞ እርስዎ ይህን መረጃ እንዴት ማግኘት እንደሚችሉ ይገልፃል። **እባክዎን በጥንቃቄ ይገንዘቡት።**

ክፍል 1 የእርስዎን መብቶች ይገልፃል፣ ክፍል 2 የኛን የጤና መረጃ አጠቃቀም እና ይፋ አደራረግን ይገልፃል፣ ክፍል 3 የአበረታች እና አደንዛዥ ንጥረነገሮች መጠቀም ችግር መረጃ አጠቃቀም እና ይፋ አደራረግን ይገልፃል፣ ክፍል 4 የኛን ኃላፊነቶች ይገልፃል እንዲሁም ደግሞ ክፍል 5 ስለ ተጨማሪ መረጃ ነው።

## ክፍል 1: የእርስዎ መብቶች

**የእርስዎን መረጃ በተመለከተ፤ እርስዎ አንዳንድ መብቶች አለዎት። ይህ ክፍል የእርስዎን መብቶች እና እኛ እርስዎን ለማገዝ ያለብንን አንዳንድ ኃላፊነቶችን ይገልፃል።**

### የጤና መረጃ ቅጂ ማግኘት

- እኛ ስለእርስዎ ያለን የጤና መረጃ ለማየት ወይም ቅጂውን ለመውሰድ መጠየቅ ይችላሉ። ይህን እንዴት ማድረግ እንደሚችሉ ይጠይቁን።
- የእርስዎን የጤና መረጃ ቅጂ ወይም የተጨመቀ መረጃ እርስዎ ጥያቄ ባቀረቡ በ 30 ቀናት ውስጥ እንሰጥዎታለን። ምክንያታዊ የሆነ፣ ወጪን-ያገናዘበ ክፍያ ልናስከፍልዎት እንችላለን።

### የጤና መረጃን ለመስተካከል መጠየቅ

- የተሳሳተ ወይም ያልተሟላ ነው ብለው ካሰቡ፤ የእርስዎን የጤና መረጃ እንድናስተካክል ሊጠይቁን ይችላሉ። ይህን እንዴት ማድረግ እንደሚችሉ ይጠይቁን።
- ላቀረቡት ጥያቄ "አይሆንም" ልንል እንችላለን፤ ነገር ግን ለምን እንደሆነ በ 60 ቀናት ውስጥ በፅሁፍ እናስታውቅዎታለን።

### ሚስጥራዊ ግንኙነቶችን መጠየቅ

- እርስዎን በአንድ በተለየ ሁኔታ እንድናገኝዎት መጠየቅ ይችላሉ (ለምሳሌ፤ በቤት ወይም በመስሪያ ቤት ስልክ) ወይም ወደ ሌላ አድራሻ መልዕክት እንድንልክልዎት።
- ማነኛውንም ምክንያታዊ ጥያቄዎችን ከግንዛቤ ውስጥ እናስገባለን በተጨማሪም እንዲያ ካላደረግን አደጋ ላይ እንደሚወድቁ ከነገሩን "እሺ" ማለት ይኖርብናል።

### እኛ ምን መጠቀም ወይም ማጋራት እንዳለብን ለመገደብ ጥያቄ ማቅረብ

- ለህክምና፣ ለክፍያ ወይም ለራሳችን ስራ ሲባል የእርስዎን የጤና መረጃ እንዳንጠቀም ወይም እንዳናጋራ መጠየቅ ይችላሉ። ከእርስዎ ጥያቄ ጋር ለመስማማት ግዴታ የለብንምና የእርስዎን እንክብካቤ የሚጎዳ ከሆነ "አይሆንም" ማለት እንችላለን።
- የእርስዎን የአበረታች እና አደንዛዥ ንጥረነገሮች መጠቀም ችግር የሚመለከት መረጃ ካለእርስዎ የፅሁፍ ፍቃድ ለህክምና ወይም ለክፍያ ጉዳች ማጋራት አንችልም።

### መረጃ ከማን ጋር እንደተጋራን የሚገልፅ ዝርዝር ማግኘት

- እርስዎ ጥያቄ ካቀረቡበት ቀን በፊት ላሉት ስድስት ዓመታት ለምን ያክል ግዜ (ብዛት) የጤና መረጃዎን እንዳጋራን፣ ከማን ጋር እንደተጋራነው፣ እና ለምን ምክንያት እንደሆነ የሚገልፅ ዝርዝር ለማግኘት ጥያቄ ማቅረብ ይችላሉ።
- ህክምና፣ ክፍያ እና የህክምና ሂደቶችን ከሚመለከቱት ውጪ ያሉ ነገሮችንና እንዲሁም ሌሎች አንዳንድ ይፋ የሚደረጉ ነገሮችን (ለምሳሌ እርስዎ ይፋ እንድናደርግ የጠየቁን ማነኛውም ነገር) እናካትታለን። በአመት ውስጥ አንድ ዝርዝር መረጃ በነፃ እንሰጣለን፤ ነገር ግን በ 12 ወራት ውስጥ ሌላ ተጨማሪ ከጠየቁ፤ ምክንያታዊ የሆነ፣ ወጪን-መሰረት ያደረገ ክፍያ እናስከፍልዎታለን።

### የዚህን የግል ሚስጢር የመጠበቅ ማስታወቅያ ቅጂ ማግኘት

- በማነኛውም ሰዓት የዚህን ማስታወቅያ የወረቀት ቅጂ ለማግኘት ጥያቄ ማቅረብ ይችላሉ፤ ማስታወቅያውን በኤሌክትሮኒካዊ መንገድ እንዲደርስዎት ተስማምተው ቢሆኑም እንኳ። ወድያውኑ የወረቀት ቅጂውን እናቀርብልዎታለን።

### ሌላ ሰው እርስዎን እንዲወክልዎት መምረጥ

- እርስዎ የጤና እንክብካቤ ጥብቅና ለሌላ ሰው ሰጥተው ከሆነ ወይም ደግሞ አንድ ሰው የእርስዎ ህጋዊ ሞግዚት ከሆነ፤ ያ ሰው የእርስዎን መብቶች መተግበር እና የእርስዎን የጤና መረጃ የሚመለከቱ ምርጫዎችን መወሰን ይችላል።
- ማነኛውም እርምጃ ከመውሰዳችን በፊት፤ ያ ሰው ስልጣን እንዳለው እና እርስዎን መወከል ይችል እንደሆነ እናረጋግጣለን።

### መብቶችዎ ተጥሰዋል ብለው የሚያምኑ ከሆነ ቅሬታ ማቅረብ

- እኛ የእርስዎን መብቶች ጥሰናል ብለው የሚያምኑ ከሆነ በገፅ 3 ያለውን መረጃ ተጠቅመው ቅሬታ ማቅረብ ይችላሉ።
- ለኪንግ ካውንቲ የማህበረሰብ እና ሰብአዊ አገልግሎት ክፍል የግል ሚስጢር መጠበቅ መኮንኑ ወደዚህ 401 Fifth Avenue፣ Suite 400፣ Seattle፣ WA 98104 አድራሻ ደብዳቤ በመላክ ወይም ለዩ.ኤስ የጤና እና ሰብአዊ አገልግሎት ክፍል የሲቪል መብቶች ፅህፈት ቤት ወደዚህ አድራሻ 200 Independence Avenue S.W.፣ Washington, D.C. 20201 ደብዳቤ በመላክ፣ በዚህ የስልክ ቁጥር በመደወል 1-877-696-6775 የሚከተለውን ድህረገፅ በመጎብኘት www.hhs.gov/ocr/privacy/hipaa/complaints/ ቅሬታ ማቅረብ ይችላሉ።
- ቅሬታ በማቅረብዎ ምክንያት ትቃት አናደርስብዎትም።

## ክፍል 2: የእኛ የጤና መረጃ አጠቃቀም እና ይፋ አደራረግ

**እንዴት ነው የእርስዎን የጤና መረጃ የምንጠቀመውና የምናጋራው?**
**እየተሰጥዎት ያለውን የጤና እንክብካቤ ህክምና ለማገዝ**

- የእርስዎን የጤና መረጃ ልንጠቀምና እርስዎን እያከሙ፣ ህክምናዎን እያቀናጁ እና እርስዎ ቤት እንዲያገኙ (መኖርያ ቤት ከሌለዎት) እያገዙ ካሉ ባለሙያዎች ጋር ልናጋራው እንችላለን።

  *ለምሳሌ: አንድ የጤና አገልግሎት ሰጪ፣ እኛ ወጪውን ለመሸፈን እንድናመቻች እና ሌላ ተጨማሪ አገልግሎት ማስተባበር እንዲቻለን የእርስዎን የህክምና አገልግሎት የሚመለከት መረጃ ይልክልናል።*

**ድርጅታችንን ለማስኬድ**

- ድርጅታችንን ለማስኬድ እና አስፈላጊ ሲሆን ደግሞ እርስዎን ለማግኘት የእርስዎን መረጃ ልንጠቀም እና ይፋ ልናደርግ እንችላለን።

  *ለምሳሌ: ለእርስዎ የተሻለ አገልግሎት ለማዳበር እርስዎን የሚመለከት የጤና መረጃ እንጠቀማለን።*

**የህክምና አገልግሎቶችዎን ለመክፈል**

- ለእርስዎ የህክምና አገልግሎቶች ስንከፍል፣ የእርስዎን መረጃ ልንጠቀም እና ይፋ ልናደርግ እንችላለን።

  *ለምሳሌ: እርስዎ ላገኟቸው አገልግሎቶች ስለተደረገ ክፍያ፣ ከዋሽንግተን ስቴት የማህበራዊ እና ጤና አገልግሎቶች ክፍል እንዲሁም ከጤና ጥበቃ ባለስልጣን ጋር እርስዎን የሚመለከት መረጃ እንጋራለን።*

**የጤና መረጃዎን የምንጠቀምበት ወይም የምናጋራበት ሌላ መንገድ ምንድን ነው? መረጃዎን በሌላ መንገድ ለማጋራት ይፈቀድልናል ወይም እንገደዳለን። አብዛኛውን ግዜ ለብዙኋኑ ህዝብ በሚጠቅሙ መንገዶች፣ ለምሳሌ ለማህበረሰብ ጤና እና ምርምር። ለእነዚህ ተግባራት ሲባል የእርስዎን መረጃ ከማጋራታችን በፊት፣ በህጉ ውስጥ ያሉ ብዙ ቅድመ ሁኔታዎችን ማሟላት ይኖርብናል። ለበለጠ መረጃ የሚከተለውን ይመልከቱ:**
www.hhs.gov/ocr/privacy/hipaa/understanding/consumers/index.html.

**የማህበረሰብ ጤና እና የደህንነት ጉዳዮች ላይ እገዛ ለማድረግ**

ቀጥለው ለተዘረዘሩት አንዳንድ ሁኔታዎች ሲባል፣ እርስዎን የሚመለከት የጤና መረጃ ልናጋራ እንችላለን:

- በሽታ ለመከላከል።
- ከባድ የሆነ የመድሃኒት ግብረመልስን ሪፖርት ለማድረግ።
- ደርሷል ተብሎ የተጠረጠረን፣ ጥቃት፣ ማግለል፣ ወይም የቤተሰብ ውስጥ ጥቃትን ሪፖርት ለማድረግ።
- ማንኛውም ሰው ጤና ላይ የተጋረጠን አደገኛ ስጋት ለመከላከል ወይም ለመቀነስ።

**ምርምር ለመስራት**

መረጃዎን ለጤና ምርምር ተግባራት ልንጠቀምበትና ልናጋራ እንችላለን።

**ከህግ ጋር ለመስማማት**

የስቴት ወይም የፌደራል ህግ ከጠየቀ፣ እንዲሁም ደግሞ እኛ ከፌደራል የግል ሚስጥር አጠባበቅ ሕጉ ጋር በሚስማማ መልኩ እየሄድን እንደሆነ ለማየት ከፈለገ፣ ከጤና እና ሰብኣዊ አገልግሎት ክፍሉ ጋርም ጭምር እርስዎን የሚመለከት መረጃ እናጋራለን።

**የሰውነት አካል እና የቲሹ ስጦታን የሚመለከቱ ጥያቄዎችን ለመመለስ እና ከህክምና መርማሪ ወይም የቀብር አስፈፃሚ ጋር ለመስራት**

- እርስዎን የሚመለከት የጤና መረጃ የሰው አካላት ከሚወስዱ ድርጅቶች ጋር ልናጋራ እንችላለን።
- አንድ ግለሰብ በሚሞትበት ግዜ፣ የጤና መረጃን ከአሟሟት መርማሪ፣ ከህክምና መርማሪ እና ከቀብር አስፈፃሚ ጋር ልናጋራ እንችላለን።

**ለሰራተኞች ካሳ፣ ለህግ አስፈፃሚ እና ሌላ የመንግስት ጥያቄዎች ምላሽ ለመስጠት**

እርስዎን የሚመለከት የጤና መረጃ ለእነዚህ ጉዳዮች ልናጋራ እንችላለን:

- ለቀረቡ የሰራተኖች ካሳ ጥያቄዎች።
- ለህግ አፈፃፀም ተግባራት ወይም ለህግ አስፈፃሚ ባለስልጣን።
- በህግ ለተፈቀዱ እንቅስቃሴዎች፣ ከጤና ቁጥጥር ኤጀንሲዎች ጋር።
- ለሀገር መከላከያ፣ ብሄራዊ ደህንነት እና ፕሬዝዳንታዊ የመከላከል አገልግሎቶችን ለመሳሰሉ ልዩ የመንግስት ተግባራት።

**ለፍርድ እና ህጋዊ እርምጃዎች መልስ ለመስጠት**

የፍርድቤትን ወይም አስተዳደራዊ ትዕዛዝን ወይም ደግሞ ለቀረበ የምስክርነት መጥርያ ምላሽ ለመስጠት እርስዎን የሚመለከት የጤና መረጃ ልናጋራ እንችላለን።

**ለሌሎች አጠቃቀሞችና ይፋ አደራረጎች**

ለስነልቦና ህክምና ማስታወሻዎች ሲባል ይፋ ማድረግ፣ ለገበያ ተግባራት ሲባል ይፋ ማድረግ፣ የተጠበቀን የህክምና መረጃ መሸጥን የሚያካትት ይፋ አደራረጎች የእርስዎ ይሁንታ ያስፈልጋቸዋል። ሌሎች እዚህ ማስታወቂያ ላይ ያልተገለጹ አጠቃቀሞችና ይፋ አደራረጎች በእርስዎ የፅሁፍ ስምምነት ብቻ የሚደረጉ ይሆናል።

## ክፍል 3: የአበረታች እና አደንዛዥ ንጥረነገር መጠቀም ችግር የሚመለከት መረጃ አጠቃቀማችን እና ይፋ አደራረጋችን

የአበረታች እና አደንዛዥ ንጥረነገር መጠቀም ችግር የሚመለከት መረጃ ሚስጥራዊነት ከአብዛኞቹ አጠቃላይ የጤና መረጃዎች አጠባበቅ በላቁ ጥብቅ ደንቦች ነው ከለላ የሚደረግለት። ለምሳሌ፣ የእርስዎን የአበረታች እና አደንዛዥ ንጥረነገር መጠቀም ችግር የሚመለከት መረጃ ካለእርስዎ የፅሁፍ ስምምነት ለህክምና ወይም ለክፍያ ተግባራት ሲባል ማጋራት አንችልም።

ካለእርስዎ የፅሁፍ ስምምነት የእርስዎን የአበረታች እና አደንዛዥ ንጥረነገር መጠቀም ችግር የሚመለከት መረጃ ለማጋራት ቀጥለው በተዘረዘሩት መንገዶች በፌደራል ሕጉ ይፈቀድልናል ወይም ይጠበቅብናል:

- በድንገተኛ የህክምና ሁኔታ ለህክምና ባለሙያ።
- ደርሷል ተብሎ የተጠረጠረን ህፃን ልጅ ላይ የደረሰ ጥቃት ወይም ማግለልን ሪፖርት ለማድረግ ለሚመለከታቸው ባለስልጣናት።
- የተጠረጠረ የወንጀል ተግባርን ሪፖርት ለማድረግ።
- ለምርምር፣ ኦዲት ወይም ግምገማ ተግባራት።
- በፍርድቤት ትዕዛዝ በተፈቀደው መሰረት።
- ብቁ ከሆነ አገልግሎት ሰጪ ድርጅት ጋር ለተደረገ ስምምነት ሲባል።

ሌሎች እዚህ ማስታወቅያ ላይ ያልተገለጹ የእርስዎን የአበረታች እና አደንዛዥ ንጥረነገር መጠቀም ችግር የሚመለከት መረጃ አጠቃቀሞችና ይፋ አደራረጎች በእርስዎ የፅሁፍ ስምምነት ብቻ የሚደረጉ ይሆናል።

የፌደራል ህጉ እና ደንቦችን በመርሃግብር መጣስ ወንጀል ነው። የተጠረጠሩ ጥሰቶች ከፌደራል ደንቦች ጋር በሚስማማ መልኩ ተገቢ ለሆኑ ባለስልጣናት ሪፖርት ሊደረጉ ይችላሉ።

**ክፍል 4: የኛ ኃላፊነቶች**

- የእርስዎን ከለላ የሚደረግላቸው የጤና መረጃዎች ሚስጥራዊነትና ደህንነት የመጠበቅ ሕጋዊ ኃላፊነት አለብን።
- የእርስዎን መረጃ ሚስጥራዊነት ወይም ደህንነት አደጋ ላይ የሚጥል ችግር ከተፈፀመ ወድያውኑ እንዲያውቁ እናደርጋለን።
- በዚህ ማስታወቂያ ላይ የተገለፁ ግዴታዎችንና ሚስጥር የመጠበቅ ተግባራትን መከተል እንዲሁም ደግሞ ቅጂውን መስጠት ይኖርብናል።
- እርስዎ በፅሁፍ እንዲያ ማድረግ እንደምንችል ካልነገሩን በስተቀር፤ እዚህ ከተገለጸው ውጪ የእርስዎን መረጃ አንጠቀምም ወይም አናጋራም። እንዲያ ማድረግ እንደምንችል ነግረውን ከሆነ፤ በማነኛውም ሰዓት ሃሳብዎን መቀየር ይችላሉ። ሃሳብዎን ከቀየሩ በፅሁፍ ያሳውቁን።

**እዚህ ማስታወቂያ ላይ ባሉት ስምምነቶች ላይ የሚደረጉ ለውጦች**

የዚህን ማስታወቂያ ስምምነቶች መቀየር እንችላለን፤ እንዲሁም ደግሞ ለውጦቹ ባለን ሁሉ እርስዎን ሚመለከት መረጃ ላይ ተግባራዊ ይሆናል። አዲሱ ማስታወቂያ ጥያቄ ሲቀርብ ሊሰጥ ይችላል እና ደግሞ በድረገፃችን ላይ ይኖራል እንዲሁም አንድ ቅጂ ወደእርስዎ እንልካለን። ለበለጠ መረጃ የሚከተለውን ይመልከቱ: www.kingcounty.gov/healthservices/MentalHealth.aspx.

**ክፍል 5: ተጨማሪ መረጃ**

ለበለጠ መረጃ የሚከተለውን ይመልከቱ:

- www.hhs.gov/ocr/privacy/hipaa/understanding/consumers/noticepp.html.
- 42 U.S.C. 290dd-3 እና 42 U.S.C. 290ee-3 ለፌደራል ሕጎች እና 42 CFR ክፍል 2 ለፌደራል ደንቦች።

**የኪንግ ካውንቲ የማህበረሰብ እና ሰብአዊ አገልግሎቶች ክፍል**
**የባህሪ ጤና እና ማገገምያ ክፍል**
**የግል ጉዳይ መኮነን (206)-263-9000**
**401 Fifth Avenue Suite 400, Seattle, WA 98104**